የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፲ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 27
ADDIS ABABA 19th March 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፳፻፮ ዓ.ም
የማዕድን ሥራዎች (ማሻሻያ) አዋጅ ......................................................ገጽ ፯ሺ፪፻፺፮

CONTENTS

Proclamation No. 816/2013
Mining Operations (Amendment) Proclamation ......................................................... Page 7296

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፳፻፮

## የማዕድን ሥራዎች አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የማዕድን ሥራዎች አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የማዕድን ሥራዎች (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፲፮/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፳፻፪ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

"፪) 'ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ' ማለት አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን እና ተቀጣሪ ሰራተኛ የማይሳተፍበት የግለሰቦች ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚከናወን የማዕድን ማምረት ስራ ነው፤"

## PROCLAMATION No.816/2013

## A PROCLAMATION TO AMEND THE MINING OPERATIONS PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Mining Operations Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Mining Operations (Amendment) Proclamation No. 816/2013".

2. <u>Amendment</u>

The Mining Operations Proclamation No. 678/2010 is hereby amended as follows:

1/ sub-article (2) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2) 'artisanal mining' means a mining operation carried out by individuals or small and micro enterprises which is mostly of manual nature and does not involve the engagement of employed workers;"

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፱) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል:-

"ሀ) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውል የጂኦተርማል ውሃ እና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ውሃ በስተቀር ሌላውን ውሃ፤"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳) ተተክቷል:-

"፳) 'የማምረት ፈቃድ' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የከፍተኛ ደረጃ፣ የአነስተኛ ደረጃ፣ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ነው፤"

፬/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፵፩)፣ (፵፪)፣ (፵፫) እና (፵፬) ተጨምረዋል:-

"፵፩/ 'ፈቃድ ተፈጻሚ የሆነበት ቀን' ማለት የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጠያቂው እና ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ማምረት ስምምነት የተፈራረሙበት ቀን ሲሆን ለሌሎች የማዕድን ሥራዎች ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ ደብዳቤ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተፈረመበት ቀን ነው፤

፵፪/ 'የማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ' ማለት መንግሥት ከማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሰበሰበውን ገቢ እና የማዕድን አምራች ባለፈቃድ ለመንግስት የከፈለውን ማንኛውንም ክፍያዎች ለሕብረተሰቡ ማሳወቅ እንዲቻል በመንግስት፣ በማዕድን አምራች ኩባንያዎች እና በሲቪል ማህበረሰብ የጋራ ጥምረት የተቋቋመ አካል ነው፤

፵፫/ 'የማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ' ማለት ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣንና ባለፈቃዱ የማዕድን ማምረት ውል ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ የምርት ሥራው እስከሚጀመርበት ጊዜ ድረስ እንደ ማዕድኑ አይነትና ፀባይ ማዕድኑን ለማምረት አስፈላጊ የሆኑ ወደ

2/ paragraph (a) of sub-article (19) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (a):

"a) water other than geothermal water that may be used for bathing, recreational and therapeutic purpose or water used for the extraction of any mineral such as brine;"

3/ sub-article (20) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (20):

"20) 'mining license' means large scale, small scale, special small scale or artisanal mining license issued pursuant to this Proclamation;"

4/ the following new sub-article (41), (42), (43) and (44) are added under Article 2 of the Proclamation:

"41/ 'effective date of a license' means the date where the applicant for a mining license and the Licensing Authority sign a mining agreement or, where it relates to other mining operation license, the date the Licensing Authority sign the authorization letter;

42/ 'extractive industry transparency initiative' means a coalition of government, mining companies and civil societies established to disclose to the public the revenue government received from mining license holders, and the amount of all payments made by the mining license holders to the government;

43/ 'mining development period' means the period between the Licensing Authority and the mining license holder sign a mining agreement and the commencement of the mining, during which the construction and development works required to open the mine, extract, crush,

ማዕድን ክምችቱ ለመድረስ፣ ማዕድን አዘሉን አካል ለማውጣት፣ ለመፍጨት፣ ለማበልጸግ፣ ማዕድኑን ለማምረት እና ለማዕድን ማምረት ሥራው አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግንባታዎች የሚከናወኑበት የዝግጅት ጊዜ ነው፤

፵፬/ 'ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ' ማለት የባህላዊ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የጌጣጌጥ ማዕድን ወይም ከደለል ክምችት የሚገኝ የወርቅ፣ የብር፣ የፕላቲኒየም ወይም የታንታለም ማዕድን እያመረቱ ያሉና የገንዘብ አቅማቸው ዘመናዊ የማምረቻ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማምረት በሚያስችላቸው ግለሰቦች ወይም የአነስተኛና የጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፴፭) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከናወን የማዕድን ማምረት ሥራ ነው።"

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፮) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) ሆነው የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል:-

"፭/ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሐ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተተክቷል:-

"ሐ) ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ወይም የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ሲሆን ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሰው ወይም አግባብ ባለው የአነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ህግ መሠረት ያልተመዘገቡ የሰዎች ስብስብ።"

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፪ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል:-

"፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ከፈቃድ ክልሉ ላይ የተወሰነው ክፍል ሳይለቀቅ በሚከተሉት ሁኔታዎች የምርመራ ፈቃድ እድሳት ሊፈቅድ ይችላል:-

concentrate and produce the mineral and other construction works that provide support to the mining are executed depending on the nature and characteristics of the mineral;

44/ 'special small scale mining' means mining operation of gemstones or placer resources of gold, silver, platinum or tantalum of which the annual run-of-mine does not exceed the limit stated in paragraph (a) of sub–article (35) of this Article, which is carried out by individuals or small and micro-enterprises who were the holders of artisanal mining license and have sufficient financial capacity to employ modern machineries and equipment in such operation."

5/ sub-article (5) and (6) of Article 9 of the Proclamation are renumbered as sub-article (6) and (7), respectively, and the following new sub-article (5) is added:

"5/ special small scale mining license;"

6/ paragraph (c) of sub-article (3) of Article 11 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraph (c):

"c) a non-citizen of Ethiopia or a group of persons who are not registered as a small and micro-enterprise in accordance with the relevant law where it is for artisanal or special small scale mining."

7/ the following new sub-article (3) and (4) are added under Article 22 of the Proclamation:

"3/ Notwithstanding sub-article (1) and (2) of this Article, the Licensing Authority may allow renewal of an exploration license without relinquishment of a portion of the license area:

ሀ) ማንኛውም የምርመራ ሥራ ባለፈቃድ ባከናወነው የምርመራ ሥራ የማዕድን ክምችት ማግኘቱን አረጋግጦ የምርት ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ለማቅረብ የቅድመ አዋጭነት ወይም የአዋጭነት ጥናት ማከናወን እንደሚያስፈልገው ሲያመለክት፤ ወይም

ለ) ማንኛውም የምርመራ ሥራ ባለፈቃድ በደንብ በሚወሰነው መሠረት ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት የምርመራ ስራውን በጸደቀው የስራ ፕሮግራም መሰረት ማከናወን ሳይችል ሲቀር፤ ሆኖም ባለፈቃዱ የሁኔታውን መከሰት በጽሑፍ ማሳወቅና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ማግኘት አለበት።

፬/ የምርመራ ፈቃድ እድሳት፦

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ፤ ወይም

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት ሲሆን ከአንድ ጊዜ በላይ፤

ሊፈቀድ አይችልም።"

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተተክቷል፦

"፪/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፦

ሀ) ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ የማዕድን ማምረት ሥራውን መጀመር፤ እና

ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር፤

አለበት።

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንደ ማዕድኑ አይነት፣ የማዕድኑ ክምችትና የማዕድን ሥፍራው ሁኔታ እያየ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) የተመለከተውን ጊዜ በደንብ የሚወሰነውን መስፈርት ተከትሎ በሚደረገው የማዕድን ስምምነት ውስጥ ሊያራዝመው ወይም ሊያሳጥረው ይችላል።"

a) where the licensee applies for and able to prove a discovery of mineral deposits and the need to undertake pre-feasibility or feasibility study to apply for mining license; or

b) where the licensee is unable to undertake the exploration activity in accordance with the approved work program due to reasons beyond his control as defined by regulation; provided, however, that the licensee shall notify in writing the occurrence of such circumstances and get the acceptance of the Licensing Authority.

4/ The renewal of an exploration license may not be allowed:

a) more than twice, in the case of paragraph (a) of sub-article (3) of this Article; or

b) more than once, in the case of paragraph (b) of sub-article (3) of this Article."

8/ sub-article (2) of Article 30 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2) and (3):

"2/ The holder of a small scale or large scale mining license shall:

a) commence mining within two years from the effective date of the license; and

b) comply with terms and conditions of the license.

3/ The Licensing Authority may, by taking into account the nature of the mineral, the mineral deposit and the mine site and following the criteria determined by regulation, conclude a mining agreement by extending or shortening the period referred to in sub-article (2)(a) of this Article."

፱/ በአዋጁ ከአንቀጽ ፴፪ እስከ አንቀጽ ፹፫ ያሉት እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፴፬ እስከ አንቀጽ ፹፭ ሆነው የሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፴፪ እና አንቀጽ ፴፫ ተጨምረዋል፡-

"፴፪. <u>ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ስለመስጠት</u>

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡-

ሀ) የቀረበው የስራ እቅድ ተቀባይነት ካገኘ፣

ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ስራ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅም ያለው መሆኑን ካረጋገጠ፣

ሐ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፣ እና

መ) አመልካቹ በጌጣጌጥ ማዕድናት ወይም ከደለል በሚገኝ የወርቅ፣ የብር፣ የፕላቲኒየም ወይም የታንታለም ባህላዊ የማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ የነበረው እና የዚሁን ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ፡፡

፴፫. <u>ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት</u>

፩/ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ጊዜ ጸንቶ ይቆያል፡ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ፲ ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፪/ ልዩ አነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል፡፡

9/ the articles from Article 32 to Article 83 of the Proclamation are renumbered to Article 34 to Article 85, respectively, and the following new Article 32 and Article 33 are added:

"32. <u>Granting Special Small Scale Mining License</u>

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive special small scale mining license where:

a) the proposed work program is approved;

b) the applicant proves that he has financial capacity to conduct the proposed mining operation;

c) the environmental impact assessment has been approved; and

d) the applicant was holder of artisanal mining license that engage in the mining of gemstones or placer gold, silver, platinum or tantalum and is not in contravention of any obligations related to it.

33. <u>Duration and Renewal of Special Small Scale Mining License</u>

1/ Special small scale mining license shall be valid for the period specified in the license; provided however, that such period may not exceed 10 years.

2/ Special small scale mining license may be renewed for a period not exceeding five years each subject to sub-article (3) of this Article.

፫/ ልዩ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችን ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈፀመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡"

፲/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፬ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ንዑስ አንቀጽ (፫) እና ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክተዋል፡-

"፫/ የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለፀው ዘመን የፀና ይሆናል፡ ሆኖም ይህ ዘመን ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም፡፡

፬/ የባህላዊ ማዕድን ሥራ ፈቃድ አይታደስም፡፡"

፲፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ሥር የሚከተሉት አዲስ ፊደል ተራ (ነ) እና (ኘ) ተጨምረዋል:-

"ነ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ያመረተውን የማዕድን ዓይነትና መጠን እያንዳንዱ ወር ባለቀ በ፲ ቀናት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርት የማድረግ እና በእያንዳንዱ የበጀት ሩብ ዓመት ያመረተውን ማዕድን የበጀቱ ሩብ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ከ፴ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመሸጥና ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማሳወቅ፤

ኘ) የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ሲሆን የኢትዮጵያ ማዕድን ኢንዱስትሪ ግልጽነት ኢኒሼቲቭ አባል የመሆን እና ለመንግስት ገቢ ያደረገውን ገንዘብ ለሕዝብ ግልጽ የማድረግ፡፡"

3/ Special small scale mining licensee shall have the right to renew the license, provided that he has fulfilled the obligations specified in the license, and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives which constitute grounds for suspension or revocation of the license."

10/ sub-article (3) and (4) of Article 34 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) are deleted and replaced by the following new sub-article (3) and (4):

"3/ An artisanal mining license shall be valid for the period specified in the license, provided however, that such period may not exceed two years.

4/ Artisanal mining license shall not be renewed."

11/ the following new paragraph (m) and (n) are added under sub-article (l) of Article 36 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article):

"m) report to the Licensing Authority the quantity and type of mineral mined each month within 10 days from the end of such month and sell the minerals mined every financial quarter within 30 days from the end of each financial quarter and notify same to the Licensing Authority;

n) in the case of a small scale or large scale mining license holder, be a member of the Ethiopian Extractive Industry Transparency Initiative and to disclose to the public the payments effected to the government."

፲፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፵ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ ከቅኝትና ይዞ ከመቆየት ፈቃዶች በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ሊተላለፍ ይችላል፤ ሆኖም የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ በውርስ ካልሆነ በስተቀር ሊተላለፍ አይችልም።"

፲፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡-

"፫/ ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱትን ማዕድናት በአገር ውስጥ ወይም ወደውጭ አገር በመላክ መሸጥ ይችላል፤ ሆኖም በወርቅ ወይም በብር ማዕድናት ማምረት ሥራ ላይ የተሠማራ የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ማዕድናት ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ምርቱን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መሸጥ አለበት።"

፲፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፩፣ ፶፪ እና ፶፫ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥራቸው እንደተስተካከለው) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ፶፩፣ ፶፪ እና ፶፫ ተተክተዋል፡-

"፶፩. <u>የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩/ በማዕድን ዘርፍ የማማከር ወይም እንደ ድሪልንግ ወይም የላብራቶሪ የቴክኒክ አገልግሎት በመሳሰሉት ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የማመልከቻ ፎርም በመሙላት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል።

12/ sub-article (1) of Article 40 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Any license, other than reconnaissance and retention may be transferred with prior consent of the Licensing Authority; provided, however, that artisanal or special small scale mining licenses may only be transferred in the case of inheritance."

13/ sub-article (3) of Article 44 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (3):

"3/ The holder of a mining license shall have the right to sell locally or export the minerals referred to in sub-article (2) of this Article; provided, however, that the holder of artisanal and special small scale mining license that has engaged in gold or silver mining shall sell the minerals produced to the National Bank of Ethiopia."

14/ Article 51, 52 and 53 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) are deleted and replaced by the following new Article 51, 52 and 53:

"51. <u>Application for Certificate of Competence for Consultancy or Technical Services</u>

1/ Any Ethiopian who wishes to engage in providing consultancy service or technical service such as drilling or laboratory service to the mining sector may apply to the Ministry for a certificate of competence by paying the appropriate application fee and completing the appropriate form

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማመልከቻውን ተቀብሎ ይመዘግበዋል፡፡

**፶፪. <u>የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

፩/ በማማከር አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያመለክት ሰው ባመለከተበት ሙያ አስፈላጊው እውቀትና የሥራ ልምድ ያለው መሆኑን ሚኒስቴሩ ሲያረጋግጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፪/ ማመልከቻው የቀረበው እንደ ድሪሊንግ ወይም ላብራቶሪ በመሳሰሉ የቴክኒክ አገልግሎት ላይ ለመሰማራት ሲሆን አመልካቹ ባመለከተበት የአገልግሎት ዘርፍ፣ አስፈላጊው የባለሙያና የማቴሪያል ዝግጅት እንዳለው በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ የጠየቀው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፫/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን፣ የሚታደስበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

**፶፫. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በምስክር ወረቀቱ ላይ በተመለከተው የማዕድን ሥራ ዘርፍ፣ የማማከር ወይም የቴክኒክ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስ ክር ወረቀት የተሰጠው ሰው በማማከር ወይም በቴክኒክ አገልግሎት ሥራው ላይ

2/ The Ministry shall accept and register the application for certificate of competence if the requirements specified in sub-article (1) of this Article are met.

**52. <u>Issuance of Certificate of Competence for Consultancy or Technical Services</u>**

1/ The Ministry shall issue a certificate of competence to an applicant where it is satisfied that the applicant has the necessary qualification and experience in the area of consultancy he wishes to engage.

2/ Where the application is submitted to engage in provision of technical services such as drilling or laboratory services, the Ministry shall issue a certificate of competence after confirming that the applicant has the necessary technical staff and equipment for the intended services.

3/ The validity, renewal and revocation of a certificate of competence shall be prescribed by regulation.

**53. <u>Rights and Obligation of a Holder of a Certificate of Competence</u>**

1/ A holder of a certificate of competence granted in accordance with sub-article (1) or (2) of Article 52 of this Proclamation shall have the right to provide the consultancy or technical service in the area of mining operation as specified in the certificate.

2/ The holder of a certificate of competence shall be required to obtain the necessary business license from the

ከመስማራቱ በፊት አግባብ ካለው የመንግሥት መስሪያ ቤት የንግድ ፈቃድ ማውጣት አለበት።"

፲፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል:-

"ሀ) የባህላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድና ልዩ የአነስተኛ ማዕድን ማምረት ስራ ፈቃድ መስጠት፣"

፲፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል:-

"ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) መሠረት በክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ከሚሰጡት በስተቀር የቅኝት፣ የምርመራ፣ ይዞ የመቆየትና የማዕድን ማምረት ፈቃዶች የመስጠት፤"

፲፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፶፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ሥር የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ተ) ተጨምሯል:-

"ተ) ከማዕድን ማምረት ሥራ የሚሰበሰበውን ገቢ ለሕብረተሰቡ ግልጽ የማድረግ።"

፲፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፷ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል:-

"፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ለሚያካሂደው የማዕድን ሥራ መሬት እንዲለቀቅለት የሚያስፈልግ ከሆነ ለሚለቀቀው መሬት ወይም ለንብረቱ የሚከፍለው ካሳ ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ ስለሚለቀቅበትና ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይሆናል።"

appropriate government office in order to provide the consultancy or technical service."

15/ paragraph (a) of sub-article (1) of Article 54 of this Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new paragraph (a):

"a) issue artisanal and special small-scale mining license;"

16/ paragraph (a) of sub-article (2) of Article 54 of this Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new paragraph (a):

"a) issue reconnaissance, exploration, retention and mining licenses other than those to be issued by a Regional State Licensing Authority under paragraph (a) and (b) of sub-article (1) of this Article;"

17/ the following new paragraph (k) is added under sub-article (4) of Article 54 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article):

"k) disclose to the public the revenue collected from mining."

18/ sub-article (1) of Article 60 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Where his mining operation requires the expropriation of land, any licensee shall pay compensation to expropriated land user and property in accordance with the appropriate law issued to compensate such expropriation."

፲፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፩ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፷፩ ተተክቷል፦

"፷፩. **<u>ካሳን አስመልክቶ ስለሚቀርብ አቤቱታና ይግባኝ</u>**

፩/ ካሳን አስመልክቶ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ የመሬት ይዞታን ለህዝብ ጥቅም ሲባል ለማስለቀቅና ለንብረት ካሳ ስለሚከፈልበት ሁኔታ ለመወሰን በወጣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ይፈጸማል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ መሬትን ካሣ በመክፈል ማስለቀቅ አስፈላጊ በሚሆን በት ጊዜ መሬትን ለሕዝብ ጥቅም ካሳ ተከፍሎ እንዲለቀቅ የማድረግ ሥልጣን ከተሰጠው መሥሪያ ቤት ጋር በመመካከር ሥራው በአፋጣኝ የሚፈፀምበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡"

፳/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፪ ንዑስ አንቀጽ (፫) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፦

"፫/ ከባህላዊ ማዕድናት ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም የማዕድን ማምረት ባለፈቃድና እንደ አግባቡ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉ እና በስምምነት በሚወሰን በፈቃድ ክልሉ አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የማህበረሰብ ልማት እቅድ መሳተፍና ለዚህ የሚያስፈልግ ወጪ መመደብ አለበት፡፡"

፳፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ(፩) ተተክቷል፦

19/ Article 61 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new Article 61:

"61. **<u>Complaint and Appeal as Regards to Compensation</u>**

1/ Any complaint or appeal related to compensation shall be determined in accordance with the appropriate law issued to govern expropriation of land holding for public purposes and payment of compensation.

2/ Where it is required to expropriate land for the purpose of mining operation the Licensing Authority shall facilitate the speedy execution of the process in collaboration with the appropriate authority empowered to expropriate land holding for public purposes and payment of compensation."

20/ sub-article (3) of Article 62 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (3):

"3/ Any mining licensee other than an artisanal mining licensee and, as appropriate, an exploration licensee shall participate in community development plan, to be determined by the license area and by agreement, and shall allocate money for such expenses."

21/ sub-article (1) of Article 63 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

“፩/ ልዩ የአነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች የማዕድን ሥራ መዝጊያ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) ፈቃዱ ሲሰረዝ፣

ለ) የማዕድን ስራው ሲቋረጥ፣

ሐ) የማዕድን ስራውን ክልል በከፊል ወይም በሙሉ ሲለቅ፣ ወይም

መ) የማዕድኑን ስራ ሲተው፡፡”

፳፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) ተተክቷል፡-

“ሀ) ለከበሩ ማዕድናት ፯ በመቶ፤”

፳፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፡-

“፫/ በባህላዊ፣ በልዩ የአነስተኛ እና በአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃዶች የሚከፈለው የሮያሊቲ መጠን በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡”

፳፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፷፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተተክቷል፡-

“፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ማዕድን ማምረት የጀመረ ባለፈቃድ ሊከፍለው የሚገባውን የሮያሊቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት እንደአግባቡ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ለሚመለከተው የክልል የበላይ ባለስልጣን ሀሳብ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡

“1/ The holder of special small scale, small scale or large scale mining license shall apply to the Licensing Authority for a mine closure certificate upon:

a) revocation of the license;

b) termination of the mining operations;

c) relinquishment of the whole or any portion of the license area; or

d) abandonment of the mine.”

22/ paragraph (a) of sub-article (2) of Article 65 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new paragraph (a):

“a) precious minerals 7%;”

23/ sub-article (3) of Article 65 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (3):

“3/ The amount of royalty payable by the holders of artisanal, special small scale and small scale mining licenses shall be determined by the laws of the Regional States.”

24/ sub-article (3) of Article 66 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (3) and (4):

“3/ Where the Licensing Authority deems it appropriate it may cause the reduction, temporary lifting or waiver of the liability to pay royalty of a licensee of an operating mine by recommending and securing approval from the Council of Ministers or the concerned higher regional authority, as the case may be.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የሮያሊቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት የሚያስችሉ ዝርዝር መስፈርቶች በደንብ ይወሰናሉ።"

፳፭/ የአዋጁ አንቀፅ ፷፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፡-

"፪/ የባህላዊ፣ ልዩ የአነስተኛ እና የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃዶች ከማዕድን ሥራ ከሚያገኙት ገቢ የሚከፍሉት የገቢ ግብር በክልል ህጎች ይወሰናል፡፡"

፳፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፪ (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፸፪ ተተክቷል፡-

"**፸፪. በመንግሥት ስለሚያዝ አክሲዮን**

፩/ መንግስት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሰረት የማዕድን ስራዎች የማካሄድ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ባለፈቃድ ከሚካሄድ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ስራዎች ኢንቨስትመንት አምስት በመቶ አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ይይዛል። እንዲሁም ስለድርሻው መቶኛ፣ ስለአከፋፈሉ፣ ከተሳትፎ ስለሚመነጩት መብትና ግዴታዎች እና ሌሎች የተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታዎች ከባለፈቃዱ ጋር በሚደረግ ስምምነት በሚወሰነው መሰረት መንግስት ተጨማሪ አክሲዮኖችን መያዝ ይችላል።

፪/ ከአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ኢንቨስትመንት መንግስት ያለምንም ክፍያ ሊይዝ የሚችለው የአክሲዮን መጠን እና የተጨማሪ አክሲዮኖች ሁኔታ በክልል ህጎች ይወሰናል።"

፳፯/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፭ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፭) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪)፣ (፫) እና (፭) ተተክተዋል፡-

4/ The detailed criteria for reducing, temporary lifting or waiver of royalty in accordance with sub-article (3) of this Article shall be determined by regulation."

25/ sub-article (2) of Article 67 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ income tax to be paid by holders of artisanal, special small scale and small scale mining licenses shall be determined by the laws of the Regional States."

26/ Article 72 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new Article 72:

"72. **Government Participation**

1/ Without prejudice to its right to undertake mining operations under Article 8 of this Proclamation, the government shall acquire without cost a participation interest of five percent of any large scale mining investment. An additional equity participation of the government may also be provided by agreement with the licensee, which shall specify the percentage, timing, financing, resulting rights and obligations and other details of such participation.

2/ The rate of government participation interest without cost and concerning additional equity participation in small scale mining shall be determined by laws of Regional Sates."

27/ sub-article (2, (3) ) and (5) of Article 75 of the Proclamation (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) are deleted and replaced by the following new sub-article (2), (3) and (5):

"፪/ ማንኛውም የልዩ አነስተኛ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉ እና በማዕድን ማምረት ስምምነቱና በጸደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት በምርት ቅድመዝግጅት ጊዜ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው መሳሪያ ዎች፣ ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም መሳሪያዎችን፣ ማሽነሪዎችንና ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነፃ የማስገባት መብት ማምረት ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ከአምስት ዓመት በኋላ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

፫/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለንግድ በሆነ መጠን ማዕድን ማምረት ከጀመረበት ቀን አንስቶ ለመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት ሊያሰራው የሚችል ማናቸውንም አላቂ ዕቃዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል፡፡

፭/ ወርቅ ወይም ብር ከሚያመርት የባህላዊ ወይም ልዩ የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም የማዕድን ማምረት ስራ ባለፈቃድ በፈቃዱ መሠረት ያመረታቸውን ማዕድናት ወደ ውጭ አገር ሲልክ አስፈላጊውን የጉምሩክ እና የባንክ ፎርማሊቲ ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ ከማናቸውም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነጻ ይሆናል፡፡"

፳፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፡-

"፪/ ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ስነስርዓት መሰረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል፡፡ በግልግል ዳኝነት የሚሰጠው ውሳኔ በተዋዋይ ወገኖች ላይ የፀና ይሆናል፡፡"

"2/ Any equipment, machinery, vehicles and consumables that any holder of a special small scale, small or large scale mining license or his contractor may import into Ethiopia and required for mining development period in accordance with the mining agreement and the approved work program shall be exempted from customs duties and taxes; provided, however, that the right to import equipment, machinery and vehicles free of customs duties and tax may not be applicable after five years starting from the date of production.

3/ The holder of a small or large scale mining license may, within the period specified in sub-article (2)(a) of Article 30 of this Proclamation, import free of customs duties consumables required to start and sustain commercial production for the first three months.

5/ Except the holder of artisanal mining license or special small scale mining license that produce gold or silver, any holder of mining license shall be entitled to export free of customs duties and taxes minerals produced according to the license."

28/ sub-article (2) of Article 78 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub article (2):

"2. In the event that agreement can not be reached through negotiations, the case shall be settled by arbitration in accordance with the procedures specified in the agreement. An arbitral award shall be binding upon the parties."

፳፱/ የአዋጁ አንቀጽ ፹፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) (በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት ቁጥሩ እንደተስተካከለው) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፡-

"፩/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ወይም የተደረገ ማንኛውም የማዕድን ማምረት ፈቃድ ወይም የማዕድን ማምረት ስምምነት ፀንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ፈቃዱ በተሰጠበት ወይም ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት ተፈፃሚ በነበረው ህግ መሠረት ባለበት ይቀጥላል። ሆኖም የፈቃዱ ወይም የስምምነቱ ዘመን አብቅቶ ሲታደስ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈፀማል።"

## ፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

29/ sub-article (1) of Article 83 (as renumbered pursuant to sub-article (9) of this Article) is deleted and replaced by the following new sub-article (1):

"1/ Any mining license or mining agreement issued or concluded prior to the coming into effect of this Proclamation shall continue in force for the remaining period of its validity in accordance with the law in force at the time of issuance of the license or conclusion of the agreement; provided, however, that the renewal of the license or agreement, upon expiry of its current term, shall be made in accordance with the provisions of this Proclamation."

## 3. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of March, 2014.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**